# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

## የ6ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ እንደአፍ መፍቻ

## ትምህርት የማጠቃለያ ፈተና ማዘጋጃ ቢጋር

ህዳር/2017 ዓ.ም

## መግቢያ

ይህ ሰነድ አራት ዋና ዋና የ6ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የማጠቃለያ ፈተና ቢጋርን የፈተና ይዘት ቢጋር፣ የክህሎት ደረጃ ቴስት ቢጋር እና የጥያቄ አይነቶች ቢጋር ናቸው፡፡የፈተና ይዘት ቢጋር ደግሞ ለፈተናው የተመረጡት ይዘቶችና ከእያንዳንዱ ይዘት የተውጣጣውን የጥያቄ ብዛት ይዟል፡፡ የክሕሎት ደረጃ ቴስት ቢጋር ዝቅተኛ የመማር ብቃትን መሰረት ያደረገ የክህሎት ክፍፍል ቀርቦበታል፡፡ እንዲሁም የጥያቄ አይነቶች ቢጋር እያንዳንዱ ይዘት በየትኛው የፈተና አይነት እንደሚካተት ቀርቦበታል፡፡

ይህ ቴስት ቢጋር የተማሪዎችን ዝቅተኛ የመማር ብቃት፣ የትምህርት ዓላማ እና የትምህርት ክፍለ ጊዜ ብዛት መሰረት በማድረግ የተዘጋጀ ነው፡፡ ስለሆነም እያንዳንዱን ይዘት በቢጋሩ ለማካተት ተሞክሯል፡፡ የጥያቄዎቹ ብዛት መሰረት የሚያደርገውም ለትምህርቱ የተሰጠውን የክፍለ ጊዜ ብዛት ነው፡፡ በዚህም መሰረት ለይዘቱ የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት ሲባዛ ጠቅላላ የጥያቄ ብዛት ሲካፈል ጠቅላላ የክፍለ ጊዜ ብዛት በሚል ቀመር ተሰልቶ ተዘጋጅቷል፡፡ ስለሆነም መምህራን ይህንን የቴስት ቢጋር ተከትለው ፈተናዎችን ቢያዘጋጁ ወጥ አሰራር እንዲኖር ያደርጋል፡፡ ቢጋሩ የተማሪዎችን የክፍል ደረጃና የሚጠበቅ ዝቅተኛ የመማር ብቃት (minimum learning competency) መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ይህንን ተከትሎም ፈተናው በሁለት መንፈቀ ዓመት ተከፍሎ ቀርቧል፡፡ ሁለቱ መንፈቀ ዓመታት እያንዳንዳቸው 40 ጥያቄዎችን የሚያካትቱ ሲሆን በድምሩ 80 ጥያቄዎችን አካትተዋል፡፡ ከጥያቄዎች አይነት አንጻር ደግሞ 5 ጥያቄዎች እውነት/ሐሰት፣ 5 ማዛመድ፣ 25 የምርጫ ጥያቄዎች፣ 3 የዳሽ ሙላ ጥያቄዎች እና 2 የሰርቶ ማሳየት ጥያቄዎች ናቸው፡፡ ከተማሪዎች ክሕሎት አንጻር ደግሞ አብዛኛዎቹ ጥያቄዎች መካከለኛ ክብደት ያላቸው ሲሆኑ ቀላል እና ከባድ ጥያቄዎች ደግሞ የተመጣጠኑ ናቸው፡፡ በዚህም መሰረት መካከለኛ ክብደት ያላቸው ጥያቄዎች (ግንዛቤን፣ መረዳትንና ትግበራን የሚጠይቁ) 20 (50%)፣ ዝቅተኛ ክብደት ያላቸው ጥያቄዎች (ማስታወስን የሚጠይቁ) 12 (30%)፣ እንዲሁም ከፍተኛ ክብደት ያላቸው ጥያቄዎች (ማሰላሰልን፣ ማደራጀትን፣ መተንተንንና መገምገምን የሚጠይቁ) 8 (20%) ናቸው፡፡

የትምህርት አይነት፡- አማርኛ

የትምህርት ዘመን፡- 2017ዓ.ም

የክፍል ደረጃ፡- 6ኛ ክፍል

የዓመቱ የክፍለ ጊዜ ብዛት፡- 180

የክፍል ጊዜ ብዛት፡- 90

| ምዕራፍ | ይዘት | የክፍለ ጊዜ ብዛት | የክህሎት ደረጃ | | | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | እውቀት | መረዳ ት | ትግበራን፣ ማደራጀትን፣ መተንተንንና መገምገምን የሚጠይቁ | |
| የመጀመሪያው መንፈቀ ዓመት | | | | | | |
| 1 | የቃላት አገባብ ስርዓትን በመከተል ዓ/ነገር መመስረት (1 ም) | 2 | | | 1 | 1 |
| | አስተካክሎ ማንበብ (2 ም) | 4 | | 2 | | 2 |
| | ለውስብስብ ቃላት ፍቺ መስጠት (2 እ) | 4 | 2 | | | 2 |
| | ስርዓተ ነጥቦችን በተገቢ ቦታቸው መጠቀም (1 ም፣ 1 ሰ.ማ) | 6 | | 1 | 1 | 2 |
| | ቃላትን እየነጣጠሉ ማንበብ (1 ም) | 2 | | 1 | | 1 |
| 2 | ከቅጥያዎች ውስጥ ዋና ቃል መለየት (1 ዳ) | 3 | | 1 | | 1 |
| | ቅጥዎችን በማጣመር ቃል መመስረት (1 ም) | 3 | | 1 | | 1 |
| | የምንባብን ዋና ሀሳብ መግለጽ (2 እ/ሐ) | 4 | 2 | | | 2 |
| | የስርአተ ነጥቦችን ትርጉም ተረድቶ የሚነሱና የሚወድቁ ድምጾችን መለየት (2 ም) | 4 | | 2 | | 2 |
| | የወል ስሞችን መለየት (2 ዳ) | 4 | | | 2 | 2 |
| 3 | አዳዲስ ቃላትን መጠቀም (1 ም) | 3 | | 1 | | 1 |
| | ግጥም ጽሮ ማንበብ (2 ም) | 4 | | 1 | 1 | 2 |
| | ቅንፍን በአረፍተ ነገር ውሰጥ መጠቀም (1 ም) | 3 | 1 | | | 1 |
| | ገላጭና ተራኪ ጽሁፎችን እና<br>የቃል ግጥሞችን ድምጽን ከፍ አድርገው ማንበብ (2 ም) | 4 | | 2 | | 2 |
| | ለቃላት ተቃራኒ ፍቺ መስጠት (1 እ) | 2 | | 1 | | 1 |
| | የጊዜ ተውሳከ ግሶችን ከዓ/ነገር ውስጥ ማውጣት (1 እ/ሐ) | 2 | 1 | | | 1 |
| 4 | አዳዲስ ቃላትን መጻፍ (1 ም) | 3 | | | 1 | 1 |
| | ቃላትን በመገጣጠም ትርጉም መስጠት (2 ም) | 4 | 2 | | | 2 |
| | አከራካሪ አንቀጽ መጻፍ (1 ም፣ 1 ሰ.ማ ) | 4 | | 1 | 1 | 2 |
| | የጊዜ ግስን ተጠቅመው ዓ.ነገር መመስረት (1 ም) | 3 | | | 1 | 1 |
| | ለአዳዲስ ቃላት ፍቺ መስጠት (2 ም) | 4 | | 2 | | 2 |
| 5 | ቃላትን በምእላድ መከፋፈል (1 ም) | 3 | | | 1 | 1 |
| | ለቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች መስጠት (2 እ) | 4 | | 2 | | 2 |
| | በሀላፊ ጊዜ አንቀጽ መጻፍ (2 እ/ሐ) | 4 | 2 | | | 2 |
| | ለአዳዲስ ቃላት ፍቺ መስጠት (2 ም) | 4 | | 1 | 1 | 2 |
| | የመገምገሚያ ስልቶችን ተጠቅሞ ራስን መገምገም (1 ም) | 3 | | | 1 | 1 |
| | ድምር | | 10 | 18 | 12 | 40 |

ማሳሰቢያ፡- ቀጥሎ የቀረቡት ቁልፍ ቃላት በሰነዱ ውስጥ የቀረቡት በአጭሩ ሲሆን ምህጻረ ቃላቱ የያዙት ፍቺ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

- ✓ እ/ሐ፡-‹እውነት› ወይም ‹ሐሰት› በማለት የሚመለሱ ጥያቄዎች = 5
- ✓ አ፡- በማዛመድ የሚመለሱ ጥያቄዎች = 5
- ✓ ም፡- ከተሰጡ አማራጮች መልሶችን በመምረጥ የሚመለሱ ጥያቄዎች = 25
- ✓ ዳ፡-ክፍት ቦታዎችን (ዳሾችን) በተገቢ ቃላት በመሙላት የሚመለሱ ጥያቄዎች = 3
- ✓ ሰ፡- የተብራራ መልስ በመጻፍ (ሰርቶ የማሳየት) የሚመለሱ ጥያቄዎች = 2